**United Ethiopian Muslims Movement (UEMM)**
**የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ንቅናቄ ሕብረት (ኢሙንሕ)**
4324 Georgia Avenue NW – Washington, DC 20011 uemm2017@gmail.com

**April 15, 2017**

# ምዕመናንን የሚያዋርድ ሥርዓት ማሳረጊያው ውርደት ነው!

በበደል መረብ አፍኖ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለ26 ዓመታት እያመሰ ያለው የወያኔ ሥርዓት የተካነበትን የወንጀል አርከን ከፍ በማድረግ በአስቸኳይ ጊዜያዊ አዋጅ ሽፋን ድብደባ፣ እሥራትና ግድያን በረቀቀ ዘዴ እያከናወነ ነው።

በጠመንጃ አፈሙዝ ታግዞ ሥልጣን የተቆጣጠረው አምባገነን ሥርዓት ገና በማለዳው በጠላትነት ፈርጆ ከዘመተባቸው መካከል የእምነት ተቋሞች ይገኙበታል። የእሥልምናና የኦርቶዶክስ ክርሥትና እምነት ተከታዮች የመጀመሪያ ሰለባዎች ነበሩ። አሁንም ናቸው። የእውቀት ባለቤት የሆኑትን የሁለቱን እምነት የሃይማኖት አባቶች ኢማሞችና ጳጳሶች ጭምር ከመንበራቸው አስወግዶ መስጊዶችንና አብያተክርስቲያናትን በካድሬዎች ያለማፈር አጭቋቸዋል። የሕዝቡን ሃብቱን፣ ንብረቱንና ሕይወቱን እንደዘረፈው ሁሉ፣ ዋናው የማንነቱ መገለጫ ሃይማኖቱ የሚጠቀምባቸውን ተቋማት ዘርፏቸዋል።

የወያኔ መሰሪ ሥርዓት በዕምነታቸው መሠረት የዚህ ዓለም ኑሮ በቃኝ ብለው ቀሪውን ሕይወታቸውን አምላካቸውን ለመገዛት ብቻ ወስነው ገዳም የገቡ መናንያን የሚኖሩበትን የዋልድባ ገዳም የጥቃቱ ዒላማ ካደረገው ዋል አደር ብሏል። በኦርቶዶክስ ምዕመናን ዘንድ ትልቅ ከበሬታና ታሪካዊ የአገር ቅርስ የሆነውን የዋልድባን ገዳም ለማፈራረስ ወያኔ ግርግር መፍጠሩ ለሃይማኖት ያለውን ጥላቻና ንቀት በአደባባይ የሚያጋልጥ ነው።

የወያኔ ሥርዓት የተያያዘውን የአገር ብተናና ዝርፊያ መገንዘብ ያልቻሉ በጎጠኝነትና በጊዜያዊ የግል ጥቅምና ምቾት እራሳቸውን አታለውና ሸንግለው ዳር የተቀመጡ ሁሉ የመባነኛና የመንቂያ ወቅታቸው አሁን ነው። ወገን በአረመኔ ሥርዓት በመከራ ሲታመስ፣ ስብእናው በቆሻሻ ሲዳፈን፣ በራሃብና በአግአዚ ጥይት እንደቅጠል ሲረግፍ የገለልተኛ አቋም መያዝ በማንኛውም መስፈርት ቢለካ ከጠላት ጎን መቆም እንጂ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም።

ፈጣሪን ተገዝተው ሃይማኖታዊ ግዳጃቸውን የሚፈፅሙትን መዕመናንን የሚደበድብና የሚያዋርድ ሥርዓት በሰውም በፈጣሪም የተወገዘና የተዋረደ ነው። ንፁህ ሕዝብ ያዘነበት እንባውን የረጨበት ሥርዓት በፈጣሪም የተጠላ እንደሆነ አያጠያይቅም።

አረመኔው ወያኔ ያልገባው ነገር ቢኖር ዋልድባ ከሃይማኖት አንፃር የክርስቲያን ወገኖቻችን ቢሆንም፣ ከታሪክና ከአገር ቅርስነት አንፃር የተለያየ እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያን ሁሉ መሆኑን ነው። ሐረር ጀጎልና የባሌው ሶፍ ኡመር ከሃይማኖት አንፃር የሙስሊሙ ቢሆኑም ከታሪክና ከአገር ቅርስነት አንፃር የሁሉም እምነት ተከታይ ኢትዮጵያዊ እንደሆኑ ሁሉ ማለት ነው። ስለዚህ ነው በአረመኔው የወያኔ ሥርዓት የዋልድባ መደፈር ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን ወደር የለለው ቁጣ እንዲሰማን ያደረገን። የወያኔ ዝቅጠት ጥልቀቱ

ወሰን የለውም። በፈጣሪያቸው ፊት አንድ የሆኑትን፣ ለአንድ ፈጣሪ የሚሰግዱትንና የሚማለሉትን የዋልድባን ምዕመናን ወያኔ ከዚህ ቀደም በካድሬዎቹ አማካይነት በዘር በመከፋፈል ሰላም ሊነሳቸው እንደሞከረ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።

በእምነታቸው ላይ የመጣውን አደጋና የገዳሙን መደፈር በመኮነን ድምፃቸውን ባሰሙት መነኩሴ በአባገብረየሱስ ላይ የተፈፀመው አፈናና ድብደባ እንዲሁም የ39 መነኮሳት በወያኔ ጦር ተንገላተው ለእሥር መዳረግን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ንቅናቄ ሕብረት በጽኑ ያወግዛል።

ክርስቲያንና ሙስሊሙን ሕብረተሰብ በሃይማኖት ከፋፍሎ ደም ለማፋሰስ በወያኔ የተጠነሰሰውን ሴራ ያከሸፈ ሕዝብ በጋራ በመቆም ወያኔ በአዲስ መልክ የጀመረውን የእምነት ማዳከምና ማራከስ ዘመቻ በማያዳግም መልኩ ማኮላሸት አለበት።

ትግላችን በአላህ ፈቃድ ድል ይቀዳጃል!

አላሁ አክበር!

የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ንቅናቄ ሕብረት


4324 Georgia Avenue NW – Washington, DC 20011 uempmsg@gmail.com